ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞክራሲያ ቅጽ 38 ቁጥር 2 ታኅሣስ/ጥር 2004 ዓ.ም

# ሕዝባዊ ትግልና ድርጅት

በአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ ሰላማዊ ተባለ የብረት ትግል የሚካሄደው ነጻነትን የተጎናፀፈ፡ መብትንም በማስከበር ክቡርነትን የተላበሰ ሰላማዊ ኑሮን ለማስፈን ነው። በሰላም በመኖር የግልንም ሆነ የሀገርን ዕጣ በጋራ በመወሰን የተስተካከለና ፍትሃዊነትን የተጎናፀፈ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ እድገትን ለማስገኘት ሲባል ነው። ትግል ስንል ሕዝብን መሠረት ያደረገና ያቀፈ፤ በሕዝብ ተሳትፎ የተደገፈ ሕዝባዊ ትግል ማለታችን እንደሆነ ደጋግመን ለመግለጽ የምንገደደውም በዚሁ ምክንያት ነው። በትግሉ ሂደትና ግለት ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ለማፍሰስ የሚጥሩ፤ ከወያኔ ጀምሮ የሱን ፈለግ በመከተል ከሕዝባችን ትከሻ ላይ ለመቆናጠጥ የሚፈልጉ ክፍሎች መኖራቸው ይታወቃል። ሆኖም እነዚህ ክፍሎች የሆነውን ዓይነት እምነት፣ ድፍረት፣ ጀግንነት፣ ሀቀኝነትና ታማኝነት ቢላበሱም፤ ከሚገባው በላይ መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ቢሆኑም፤ ጥቂቶች ብቻ ትግል አካሂደው ነፃነትንና መብትን ለሕዝብ ሊያጎናፅፉ የሚችሉበት ሁናቴ ሊኖር አይችልም። ሀገር የጥቂቶች ሳትሆን የብዙሃን ናትና! ለሀገሩ ደህንነት፣ ለብሔራዊ አንድነቱ የሕዝብ የራሱ ተሳትፎ ምንጊዜም ወሳኝ ነው። ስለዚህም በትግሉ የሕዝብ ግንባር ቀደም ተሳትፎ ካልተረጋገጠ የሚፈለገው ሕዝባዊ ድል የሚገኝበት ጊዜ ይራዘማል፤ በዛው መጠንም የሚከፈለው መስዋዕትና ዓይነቱ ይጨምራል። ይህ ደግሞ የግዴታ ካልሆነ በስተቀር ተፈላጊም አግባብነትም ያለው አይደለም። ይህንን የፖለቲካ ሀሁ እውነትነት የሚያረጋግጥ የትግል እንቅስቃሴ በተለያዩ ሀገሮች በቅርቡም ከጥቂት ወራት በፊት በሰሜን አፍሪካ በተደረጉት ሰላማዊ ሕዝባዊ አመፆች ለመታዘብ አስችሎናል። የነዚህ ሀገር የለውጥ ኃይሎች "ሰላማዊ ሕዝባዊ አመፅ ይለምልም" የሚል መፈክር ዛሬም በቀጣይነት እያስተጋቡ የሚገኙት የትግል ፍሬያቸውን እንዳይነጠቁና ተመልሰው በሌላ አምባገነን አገዛዝ መብታቸው እንዳይገፈፍ በማሰብ ነው። በድርጅት ከሚመራ የሕዝብ ትግል ውጪ የሀገርን ክብርና ሉዓላዊነት፡ የሕዝብንም መብት ማስጠበቅ አይቻልም። ስለ ትግል፣ ድርጅትና አመራር አስመልክቶ የግንዛቤ ማጣር ችግር በተደጋጋሚ እየተስተዋለ አግባብነት የሌለው ንትርክ ውስጥ እንዲገባ የበኩሉን አስተዋፅዖ እያደረገ ነውና በርዕሱ ላይ ያለንን አመለካከት ደግሞ ደጋግሞ ግልፅ ማድረግን የግድ ይላል። ይህ ሲባል ደግሞ አለምክንያት አይደለም።

ትግል ሲሉ ስንል፡ ድርጅት ሲሉ ስንል፡ አመራር ሲሉ ስንል ይባላልና ትግል ሲባል ደግሞ ሕዝብን ያቀፈ እሱንም መሰረት ያደረገና በሱ ሙሉ ተሳትፎ የሚደገፍ ማለታችን ነውና ሁሌም ወቅታዊ ሁኔታዎችን በጥሞና መርምሮ ከሌሎችና ከራሳችንም የተገኙ ተመክሮዎችን ከግንዛቤ በመውሰድ ወሳኝ በሆኑ የኤኮኖሚ፡ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ዙሪያ ሕዝብን ሊያስተባብሩ በሚችሉ መፈክሮች ሥር ማደራጀት፤ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችንም ማቀናበር፤ ማስተባበርና ማታገል ነው። ለዚህ ደግሞ ወቅታዊውን ዓለም አቀፍና ሀገራዊ የፖለቲካ፣ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ሁኔታን የሚረዳ፤ የሕዝቡን የልብ ትርታ የሚያዳምጥ፤ ሉዓላዊነቱን ከልብ የሚቀበል፤ ተጠያቂነቱ ለሕዝብ የሆነ፤ አቅጣጫን የሚጠቁመው፤ በሚያቀርባቸው ግልፅነት ያላቸው ትንታኔዎችን በማቅረብ ሕዝብ ንቃተ ሕሊናውን እንዲያዳብርና የራሱን ውሳኔ ለመውሰድ እንዲያስችለው የሚያደርግ የፖለቲካ ድርጅትን ግድ የሚል መሆኑ ደግሞ ጥያቄ የሚያጭር አይደለም። ሕዝባዊ ትግሉ ከግብ እንዲደርስ መሠረት የሚሆነው በሕብረተሰቡ ቀጥተኛ የተሳትፎ ትግል እንደመሆኑ መጠን ሕዝብን ተከተው ለመታገል የሚሹ ከወዲሁ የትግሉ እንቅፋት መሆናቸውን መገንዘቡ ጠቃሚ ነው። ሕዝባዊ ድርጅቶች ነፃነታቸውን እንዳይነጠቁ፤ የውሳኔ ተቀባይና በሥራ ተርጓሚነት ላይ ብቻ እንዳይመደቡ ሁሌም ማገዝና መደገፍ የፖለቲካ ድርጅቶች ተግባር ሆኖ የሚከሰተውም አንዱም በዚሁ ምክንያት ነው።

የፖለቲካ ድርጅት ሕዝባዊነቱን እንዲላበስ ደግሞ አባላቱ ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ብቻ ሳይሆኑ በፕሮግራሙ፣ በዕይታው፣ በእንቅስቃሴው፣ በፕሮፓጋንዳው፣ በማደራጀት ተግባሩ ለጠቅላላው ሕዝብ ጥብቅና መቆሙን የሚያንጸባርቁለት/የሚያረጋግጡለት ሊሆኑ ይገባል። ድርጅቱ በነዚሁ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚንሸራሸሩትን የተለያዩ የሕዝብ ጥያቄዎች በማንሳት ማህበራዊ አንድነታቸውን በሚያስጠብቅና በሚያረጋግጥ መልኩ መፍትሄ ለመስጠት በመጣርና በርካታውን ሕዝብ - ሰራተኛውን፡ ገበሬውን፣ ዘላኑን፣ ተማሪና አስተማሪውን፡ ጭቁን ሴቶችን፣ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችን ሁሉ - በደጋፊነት ለማሰባሰብም ጥረት ማድረግ ይኖርበታል። ሕዝብ የማይደግፈው ድርጅት ሊጠናከር አይቻለውምና ሕዝቡም በበኩሉ ይህን የመሰለ ድርጅት በቀን ተቀን እንቅስቃሴው ሊገመግመው፤ ሲሳሳት ሊያርመው፡ መልካም ሲሠራ ባለውና በሚችለው ሁኔታ ይበልጥ ሊደግፈውና ሊንከባከበው የግድ ይለዋል። በፖለቲካ ድርጅትና በሕዝብ መካከል ሊኖር የሚገባው መልካም ግንኙነት በነዚህ ላይ የሚመሰረት ነውና።

ድርጅት ሲሉ ስንል ነውና፤ ድርጅት የትግል መሳሪያ ነውና፤ ከድርጅት ውጪ ለድል የሚያበቃ ትግል አይታሰብምና፤ ዜጎች በሃሳብና በእይታም ከሚቀራረቧቸው ጋር በመቧደን የሚደራጁበትን ሁናቴ መኖሩን መገንዘብ ያስፈልጋል። ይህንን በቀላሉ በመመልከትና በሚገባም ባለመረዳት የፖለቲካ ድርጅቶች ብዛትን የሚወስነው ተጨባጩ ሁኔታና ሕዝብ መሆኑን ወደጎን በማድረግ፤ ባንድ ወቅት ለኢትዮጵያ ከአራት በላይ የፖለቲካ ደርጅት አያስፈልጋትም ከሚል ድምዳሜ አንዳንዶች መድረሳቸው እምብዛም የሚያስደንቅ ባይሆንም ለጥቂት ጊዜያት ውዥንብር የፈጠረ መሆኑ የሚረሳ አይደለም። ለዚህም ነው

በርዕሱ (በምሳሌነት የቀረቡትና ሌሎች ተመሳሳይ ያልቀረቡት) ላይ ጥራትና ግልፅነት እንዲኖር አንድ ማለቱ ዳግም የሚያሻው።

የፖለቲካ ሥልጣን ከሕዝብ ይመነጫል ተብሎ ቢነገርም ሕዝብ ይህንን ሥልጣኑን ተግባራዊ የሚያደርገው በተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶች አማካኝነት በመሆኑ የፖለቲካ ደርጅቶች ወሳኝና መሠረታዊ ናቸው። ስለሆነም የፖለቲካ ድርጅት ማለት ለተወሰኑ ስብስቦች ጥቅም ከተደራጁት ሕዝባዊ ድርጅቶች በተለየ የራሱ አወቃቀር ያለው፤ ተመሳሳይ ዓላማና ራዕይ ያላቸው ዜጎች በነፃ ፍላጎታቸው የሚሰባሰቡበትና የሚዋሃዱበትም መርሃ ግብር ያለው፤ የነደፈውን የፖለቲካ ዓላማ ከግብ ለማድረስ በሕዝብ አስተያየት ላይ የፖለቲካ ተፅዕኖዉን በማሳደር የፖለቲካ ሥልጣን ለመጨበጥ የሚንቀሳቀስ ነው። እንዲሁም ሕዝብ በፖለቲካው ተሳትፎ እንዲያደርግ በመቀስቀስ፣ በመሃላቸውም ማህበራዊና ፖለቲካዊ አንድነት እንዲገኝ ጥረት የሚያደርግ፤ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎችም የፖለቲካ ሥርዓቱ ሕጋዊነት እንዲጎናፀፍ አለበለዚያም በምትኩ አዲስ ሥርዓት እንዲመሰረት ለመታገያ የሚመሰርቱት ነው።

በአንድ ሕበረተሰብ ውስጥ የተለያዩ አስተሳሰቦች፡ ፍላጎቶችና ማህበራዊ ውጥረቶች/አለመግባባቶች ይኖራሉና አንድ አሃዳዊ የሆነ የሕዝብ ፍላጎትና ደህንነት ሊኖር እንደማይችል በርካታ ድርጅቶች የመኖራቸው ማጠየቂያም ይኸው መሆኑን መገንዘብ የግድ ይላል። በጥቅም አስጠባቂዎቹ መካከል ለሚከሰተው ውጥረት በሰላማዊ መንገድ መፍትሄ የማቅረቡ ኃላፊነት በቅድሚያ በፖለቲካ ድርጅት ላይ የሚወድቅ እንደሆነ ግልፅ ነው። ለዚህም ከሁሉ አስቀድሞ ሁሉም የጥቅም አስጠባቂ ክፍሎች ግልፅ በሆነ ውይይት ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉበትን የፍላጎት ግንባታ ሂደት ተግባራዊ እንዲሆን መሠረት በሆነው በጨዋታው ሕግ ላይ መግባባት እንዲኖር የግድ ይላል። በመሆኑም ይህንን በሚገባ ተረድቶ ለዚህ ስኬት መሰማራት የፖለቲካው ሀሁ ነው። በዚህም የተነሳ የፖለቲካ ድርጅት፤ ከተለያዩ የጥቅም ቡድኖች ጋር ዋናው ግብ ላይ እድገት ሊያስገኝ በሚችል አብረው በጋራ ሊሰሩ የሚችሉበትን ሁናቴ ሁሌም ማሰብና ማሰላሰል ይጠበቅበታል። ይህ የተለያዩ የጥቅም ክፍሎች በአደባባይ ሲወጡና ድርጅቶችም እነዚህን ጥቅሞች ለመወከል የሚችሉ ለመሆናቸው እርስ በርስ እውቅና ሲሰጡ ለችግሩ ሥርዓትን በተከተለ መልኩ ሁሉም አሸናፊ ሊሆኑ የሚችሉበት ሂደት ክፍት ይሆናል።

በዚህም ምክንያት ነው የፖለቲካ ድርጅቶች በአስተዳደሩና በሕዝቡ መካከል የመገናኛ ድልድይ ወይንም መስመር በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው ተብሎ የሚገለፀው። ይህም በመሆኑ ነው የፖለቲካ ድርጅት ነፃነትንና መብትን የግዴታ የማክበር ጥያቄ የሚቀርበውና ወሳኝነትንም የሚላበሰው። ይህ የድርጅት ነፃነት ደግሞ በአምባገነን መርህ መሠረት በቀድሞ ምሥራቅ አውሮፓና በአሁኑ ወቅት ደግሞ በተወሰኑ የእስያ ሀገራት እንደሚታየውና በሀገራችንም በደርግና አሁን ደግሞ በወያኔ ተግባራዊ ሆኖ የሚገኘው - ማንኛውም ዜጋ ያለ ፍላጎቱ በተለያዩ ተጽዕኖዎች/ጭነቶች፣ በማስፈራራት፣ በጥቅማ ጥቅሞች (ሥራ፣ ትምህርት፣ ሹመት፣ ገንዘብ...) በመደለል - በማይፈልገው በአንድ ድርጅት ውስጥ አባል አለማድረግን የሚያጠቃልል ነው።

የፖለቲካ ድርጅት ዋና ተግባር ተብለው ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱ የፖለቲካ ፍላጎትን መገንባት ሲሆን በዚህ ሁናቴ መሠረታዊ የሆነ የፖለቲካ ውሳኔ በመውሰድ ዜጎችን የፖለቲካ አቅጣጫ ይጠቁማል፡ እንዲይዙም ይቀሰቅሳል። በተለይም ዜጎች በፖለቲካ ድርጅት እንቅስቃሴ ውስጥ በራሳቸው ፍላጎት በመሳተፍ በፖለቲካው ውሳኔና ሂደት ላይ የራሳቸውን ተፅዕኖ እንዲያሳርፉ ያግዛል። በሕዝብ ሉዓላዊነት መርህ በመመሥረትም የፖለቲካ ድርጅት ሕዝቡ ሊመርጣቸው የሚችሉ እጩ ዜጎችን ለምርጫ ውድድር ያቀርባል። ሕዝብ መብቱን ተጠቅሞ የምርጫ ውሳኔውን ከመውሰድ አስቀድሞ ሊወክሉትና ሊመሩ የሚችሉ ለዚህ ብቁ ናቸው የሚባሉትን ዜጎች በድርጅቶቹ አማካኝነት ያዘጋጅላቸዋል። በዚህም የተነሳ የፖለቲካ ድርጅት ቅድሚያዊ የምርጫ ዝግጅቶችን ያከናውናል ማለት ነው።

የሕብረተሰቡን የተለያዩ ክፍሎች አባላት ማዋሃድ ሌላው የፖለቲካ ድርጅት ተግባር ነው። በሕብረተሰብ ውስጥ የተለያዩ አስተሳሰቦችና የጥቅም ግጭቶች በመኖራቸው ለተከሰቱና መፍትሄ ላልተገኘላቸው ወደፊትም ለሚከሰቱ ችግሮች ሥርዓትን በተከተለ ሁኔታ መፍትሄ ለማግኘት በማይቻልበት ወቅት ሕብረተሰቡ አንድነቱን ጠብቆ የተረጋጋና ሰላማዊ ማህበረሰብ ሊሆን ስለማይቻል የመበታተኑ አደጋ ከፍተኛ ነው። ወያኔ ተግባራዊ እያደረገ ባለው ሁናቴ የኢትዮጵያ ሕልውና አደጋ ላይ ወድቋል። የመገነጣጠል አደጋ እያንዣበበ በመሆኑ ሀገር ወዳድና ለሕዝባቸው ቀናኢ የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ከሚመዘነቡት አንዱ ለዚህ አሳሳቢ ለሆነ አደጋ በሚሰጡት መፍትሄ መሆኑ ደግሞ ግልፅ ነው። በመሆኑም የፖለቲካ ድርጅቶች ዋና ተግባር ሕብረተሰቡ እንዳይከፋፈል፣ እንዳይነጣጠል እነዚህን የተለያዩ የጥቅም ፍላጎቶች ሊጣጣሙ የሚችሉበት ሁኔታ ሳይታክት መጣር በትኩረት ከሚያስቡባቸው ክስተቶች አንዱ ነው። ይህንን አሟልተው ሲገኙ በርግጥም የሕዝባዊነትና ሀገር ወዳድነት ካባ ለመላበስ ይችላሉ። ሕዝብም የራሱ ወኪል አድርጎ ይመለከታቸዋል። በድርጅቱና በሕዝቡ መካከል ጤናማ ግንኙነት ይፈጠራል። ሕዝብም የድርጅቱን ደህንነት እንደዓይን ብሌኑ በመመልከት ይጠብቀዋል። የፖለቲካ ድርጅትና ሕዝብ በአሳና በባሕር ተምሳሌት የሚጠቀሱትም በዚሁ ምክንያት ነው።

ያለ ፖለቲካ ድርጅት ሕዝብ ፍላጎቱን ተግባራዊ ለማድረግ አይቻለውም። በፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ ነው መድበላዊ በሆነ ሕብረተሰብ ውስጥ የሚኖር ሕዝብ በውስጡ የተግባር እምቅ ኃይል የሚኖረውና ይህንንም ኃይል ነው ፍላጎቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠቀምበት። የጥቅም ድርጅቶች አንድን ዜጋ በተለያዩ ሚናዎች ሲያደራጁት የፖለቲካ ድርጅቶች ግን ዜጋን በሁለመናነቱ ኃላፊነት የሚሰማው የሕዝብ ሉዓላዊነትና የሕዝብ የሥልጣን ምንጭነት አካል አድርገው ይመለከቱታል። መድበላዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲመሠረት ትግል በሚካሄድባቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ መድበላዊ ሕብረተሰብ ዘንድ በተለያዩ ምክንያቶች በፖለቲካ ድርጅቶች እየቀረበ ያለው አግባብነት ያለውና የሌለው ጥላቻና ትችት እንዳለ ሆኖ፤ በጥሞና ለሚመለከት ማንኛውም ሀገር ወዳድ ታጋይ ያለ ፖለቲካ ድርጅቶቹ ለሕብረተሰቡ ውስብስብ ችግሮች መፍትሄ መስጠት የሚታሰብ እንደማይሆን ከግልፅም ግልፅ ይመስለናል። ይህም

በመሆኑ ነው በድርጅቶቹ ላይ የሚነዛውን ትችትና ወቀሳ በደፈናው ለመቀበል የሚያስችግረው። በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን ድክመት በመጠቀም ድርጅቶች እንደማያስፈልጉ፤ እንደማይረቡ በመስበክ ሕዝቡ በተአምር በነሱ አርቆ አስተዋይነትና ብቸኛ "ጀግና" መሪዎች እየተመራ በወያኔ ላይ ድልን እንደሚቀዳጅ ተደርጎ የሚቀርበው ስብከት፤ የግልን አስተሳሰብ በብዙሃኑ ላይ ለመጫን የሚደረግ ጎጂ ጥረት መሆኑን በመገንዘብ አጥብቆ መታገል ያሻል። ይህን የመሰለ አስተሳሰብ ዜጎች በፈለጋቸው ደረጃ የመደራጀት ነፃነታቸውን የሚገፍ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ሲሆን የማንኛውም ድርጅት ሕይወት፣ የቁጥራቸው ብዛትና በፖለቲካው መድረክ መንቀሳቀስ የሚወሰነው በግለሰብ ሳይሆን በሕዝብ ብቻ መሆኑን አለማወቅ ጭምርም ነው።

የፖለቲካ ግንባታ የሚያሳየው አንድን የፖለቲካ ፍላጎት ከመሰረቱ ከዜጎች፣ ከሕህብረተሰብ ክፍሎች አንስቶ ሕጋዊ በሆነ ምክር ቤት፣ በሕዝብ ወኪሎች አማካኝነት በሕግነት ፀድቀው ተግባራዊ እስከሚሆኑ ድረስ ያለውን የውይይት፡ የመግባባትና የመወሰን ሂደት የሚገልፅ ነው። የፍላጎት ግንባታ ደግሞ ለፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ የሚተው ሳይሆን የአሰሪና ሰራተኛ ድርጅት፣ ሕዝባዊ ድርጅቶች፣ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች፣ ምሁራኖች፣ ሊቃውንቶችና የነፃ ፕሬስ አባላት፣ በአስተዳደሩ ሥርዓት ተቋም ፍርድ ቤት ጭምር ሌሎችም እንደ አቅማቸው የየበኩላቸውን አስተዋፅዖ ሊያበረክቱ የሚችሉበት ሲሆን ነው።

በሕዝብ አስተያየት ላይ የራሱን ተፅዕኖ ለማሳደርና በፖለቲካው ፍላጎት ግንባታና ሂደት ተካፋይ ለመሆን ደግሞ የፖለቲካ ድርጅት ነፃነትን የተላበሰ፤ በተግባር፣ በተጨባጭ ዴሞክራሲያዊ ሊሆን የግድ ይለዋል። እነዚህም በሰብአዊና በዴሞክራሲያዊ መብቶች ሥር ተጠቃለው የሚገኙት:-

- ለሰብዓዊ መብት ጥብቅና መቆም፤
- የሀገር ሉዓላዊነትን ማክበርና ማስከበር፤
- የሥልጣን ክፍፍል መርህን መቀበልና ለተግባራዊነቱም ያለመታከት በቀጣይነት መታገል፤
- የመንግሥት ተጠያቂነትንና ግልፅነትን መቀበል፤
- የአስተዳደሩ ሕግን ተከትሎ መሥራትን ማስጠበቅ፤
- የፍርድ ቤት ተቋም ነፃነትን መጠበቅ፤
- ለመድበላዊ ዴሞክራሲና ሥርዓት መገንባት አበክሮ መታገል፤
- የአባል ቁጥር ብዛትና የገንዘብ ኃይል አቅም ግምት ሳይገባ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች እኩለነታቸው እንዲረጋገጥ መጣር

የተሰኙት ትግልን፣ ድርጅትንና የፖለቲካ መሪነትን አስመልክቶ ተበክረው የሚገለፁ እሴቶች ናቸው።

ለሰው ፍጡር ክቡርነትና ለሰብአዊ መብቱ መከበር ከልቡ ዕውቅና የሰጠና በቀን ተቀን ኑሮውም በዚሁ መርህ የሚመራ ብቻ ነው ለነዚህ እሴቶች ተግባራዊ መሆንና ሕይወቱንም ለመስጠት ዝግጁነት የሚያሳየው። ይህ ብቻ አይደለም። እነዚህ እሴቶች የአንድን የፖለቲካ ድርጅት ማንነት ለማወቅ፡

ከፕሮግራሙ ባሻገር ተግባሩን ለመመርመርና ለማጣራት የግድ የሚያስፈልጉት ናቸው። በተለይም አንዳንዶች ስለራሳቸው ያላቸው ግምትና የሚነዙት ፕሮፓጋንዳ ከራሳቸው እይታና ማንነት ሊጣጣም እንደማይችል ባለፉት 40 አመታት አሁንም በቅርቡ በወያኔ አገዛዝ ሥር በሚንቀሳቀሱት ውስጥ ተንፀባርቆ እየታየ ነው። በመሆኑም የፖለቲካ ድርጅት ነኝ የሚለውን ሁላ እንዳለ ሳያላምጡ መቀበልና መደገፍ ሳይሆን ፍሬውን ከገለባ ብስሉን ከጥሬው፤ ለሕዝብ መቆሙን በትግል ከሚያረጋግጠውና ከአልማጩ ብሎም የግሉን ጥቅም ብቻ ለማሳደድ የበግ ለምድ ከለበሰው ለመለየት የሚያስችሉ ናቸው። ከዚሁ ጋር ተያይዞም በርዕዮተ ዓለም በመመሥረት የሁሉንም የሕብረተሰብ ጥቅም ለማስጠበቅ ከተደራጀውና ለተወሰነ ክፍል ብቻ ጥብቅና ለመቆም ከሚታገለው ብሎም ማንኛውም ድርጅት የሚከተለውን ፖሊሲና ዓላማ ጥቅምና ጉዳቱንም በሚገባ ለመለየት የሚያስችል መሳሪያ ነው። አንድ ድርጅት ነፃነት ያለው፡ ተጠያቂነቱ ለሕዝብ የሆነ፤ የባዕዳን ጥገኛ አለመሆኑም መፈተሽ የሚቻለው ማንኛውም ዜጋ በነዚህ እሴቶች ላይ የጠራ ግንዛቤ ሲኖረው እንደሆነም ተመክሮና በርካታ ጥናቶች የሚያረጋግጡት ነው።

ለተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጥቅም መደራጀት ጥቅሙ በተለያዩ ሃሳቦች መካከል ፉክክር እንዲኖር ያደርጋል፤ ሕዝቡ ራሱ በመፍትሄ ፍለጋው ተሳታፊ ሊሆን ስለሚችልም ጥራት ያለው የመፍትሄ ሃሳቦችንም ለማቅረብ የሚያግዘው ነው። ለምሳሌ በብሔረሰብ ብቻ የተደራጀ ከራሱ መፍትሄ በስተቀር የተለየ ሌላ ምንም አይነት አማራጭ እንዲቀርብ የማይፈልግ፤ ለችግሮች መፍትሄ ሳይሆን ለራሱ ሥልጣንን ለብቻ በመያዝ ላይ ያነጣጠረ ወይንም ደግሞ ግላዊ ጥቅሙን የእይታው ዋና እምብርት የሚያደርግ ስለሚሆን ለጋራ ትግል በጣም አስቸጋሪ ለመሆኑ ያለፉት 40 አመታት በተለይም በኤርትራ የተካሄደው ትግልና ውጤት የወያኔ እንቅስቃሴና ሌሎችም ይህንን ፈለግ ተከትለው ለመሄድ የሚያደርጉት ጥረት በሚገባ የሚያሳይ ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞም የድርጅት ሥም የድርጅቱን ማንነትና ምንነት ሊገልፅ የማይችል መሆኑን ለመገንዘብ ይረዳል። በመሆኑም እነዚህ እሴቶች የፖለቲካ ድርጅትን ለመመርመር የሚያገለግሉ ብቻ ሳይሆኑ ስለ ፖለቲካ መሪነትም በርካታ ከስተቶችን የሚያስጨብጡ ናቸው። የድርጅት መኖሩ ወሳኝነቱ ከቶምና መቸም ለጥርጥር መዳረግ የለበትም። ድርጅት አስፈላጊ ነው። ብቃት ያለው ድርጅት መኖሩም የግድ ነው። ወሳኝ ጊዜ ላይ ደርሰናልና ሀቀኛ የሕዝብ ድርጅቶችን ደግፈንና አቅፈን እንታገል።

የሕዝባችንን ፍላጎትና ተስፋ ተግባራዊ እናድርግ!
የድል ዋስትና ትግል፤ የትግል ዋስትና የተጠናከረ የፖለቲካ ድርጅት!
እናቸንፋለን!!!